## 1 እግዚአብሔር ለክብሩ ፈጠረን

ወንዶች ልጆቼን ከሩቅ ሴቶች ልጆቼንም ከምድር ዳርቻ በስሜ የተጠራውን ለክብሬም የፈጠርሁትን የሠራሁትንና ያደረግሁትን ሁሉ አምጣ እለዋለሁ። (ኢሣ፤43:6-7)

የሩቅ አጉሊ መነጽር የከዋክብትን ውበት እንደሚያጎላ እኛም የርሱን ክብር እንድናጎላ እግዚአብሄር ፈጠረን። መልካምነቱ፣ እውነቱ፣ውበቱ፣ጥበቡ እና ፍጹምነቱ በኛ ውስጥ ሆኖ እንዲታዩ ፈጠረን።በአምላክነቱ ጥልቅ የሆነ ደስታ ሲሰማን የእግዚያብሄርን ክብር ማሳየት እንችላለን፡፡ይህም ማለት እግዚአብሔር ክብሩን ያገኛል፤ እኛም ደስታን እናገኛለን።እኛ በርሱ ስንረካ እርሱም በበለጠ በኛ ሊከብር እግዚአብሔር ፈጠረን።

## 2 ሁሉም ሰው ለእግዚአብሔር ክብር መኖር አለበት

እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውም ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሄር ክብር አድርጉት።1ኛ ቆሮ፤10:31

እግዚአብሄር ለክብሩ ከሠራን ለክብሩ መኖር አለብን።የሥራችንን ዕቅድ የሚመጣው ከርሱ ነው። ስለዚህ የመጀመሪያ ግዴታችን በርሱ መተማመን፣ አለኝታችን ማድረግ፣ የርሱን ታላቅነት ማሳየት እና በሆነልን ነገር ሁሉ ተደስተን መኖር ነው።ይህም ማለት እግዚብሄርን መውደድ (ማቴ 22፤37)፣ እርሱን ማመን ነው(1ኛ ዮሐ፤5፤3-4) እና ሁልጊዜም እርሱን ማመስገን (መዝ፤100:2-4) አለብን ማለት ነው፡፡ይህ የእውነተኛ መታዘዝ ሁሉ መሰረት ነው። በተለይም ሌሎችን ለመውደድ፡፡ (ቆላስ 1፤4-5)

## 3ኛ፡ ሁላችንም እግዚአብሔርን እንደሚገባ ከማክበር ጎድለናል

ሁሉም ኃጢአትን ሠርቷልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፡ ሮሜ፡3፤23

የእግዚአብሔር ክብር ጎድሎአቸዋል ማለት ምን ማለት ነው?

ማንኛችንም እግዚአብሔርን እንደሚገባ አላመነውም፡፡እንዲሁም እንደ ትልቁ ሀብታችን አልቆጠርነውም፡፡የእግዚያብሄር ታላቅነቱ ለኛ በቂ አልነበረም፡፡በመንገዱም አልተጓዝንም፡፡በሌሎች ነገሮች እራሳችንን ለማስደሰት ሞክረናል፡፡እነዛንም ነገሮች ከእግዚያብሄር የበለጠ አክብረናቸዋል፡፡

ይህም ማለት የእግዚአብሔርን ማንነት ወይም ባህሪ ንቀን ባእድ አማልክትን አምለከናል ማለት ነው (ሮሜ፤1፤21-23)፡፡ ኃጢአት ወደ ዓለም ከገባ ጀምሮ እግዚአብሔርን እንደ ብቁ ዋስትናችን አድርገን መቀበል አልቻልንም(ኤፌ፡2፤3)።

ይህም ከእግዚአብሔር ታላቅነት አንፃር አፀያፊ ድፍረት ነው (ኤርሚያስ 2:12-13)።

## 4 ሁላችንም ከእግዚአብሔር ፍጹምና ጻድቅ ፍርድ በታች ነን

የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነውና፤ሮሜ 6:23

ሁላችንም የእግዚአብሔርን ክብር አጉድለናል፤ እንዴት?

ከርሱ በላይ ሌሎች ነገሮችን በመምረጥ፣ በክፋታችን፣ እምነትን በማጉደላችን እና ባለመታዘዛችን ክብሩንአጉድለናል ።ስለዚህ እግዚአብሔር ከዘላለማዊ ክብሩ ደስታ ውጭ ቢያደርገን እውነተኛና ትክክል ነው ይገባናልና።

ከጌታ ፊት ከሀይሉም ክብር ርቀው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ 2ኛ ተሰሎንቄ 1፤9

“ሲኦል“ የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን አሥራ ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል፡፡አስራ አንዱን ጊዜ ኢየሱስ እራሱ ጠቅሶታል።በማይረባና ባበደ ሰባኪ የተተረከ አፈታሪክ አይደለም።ኃጢአተኞችን ከርግማን ሊያድን ከሞተው የእግዚአብሔር ልጅ የወጣ ከባድ ማስጠንቀቂያ ነው።

እኛ ግን እጅግ አደገኛ በሆነ ሁኔታ እያቃለልነው ነው፡፡መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው ልጅ መናገሩን እዚሁ ላይ ቢያቆም ወደ ክፉ ቅጣትና ተስፋ ወደሌለው ጨለማ እንወረወር ነበር፤ ነገር ግን እዚህ ላይ አላቆመም።

## 5 እግዚአብሔር አንድ ልጁን ኢየሱስን የዘላለም ህይወትና ደስታን ይሰጠን ዘንድ ላከ

ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው። 1ኛ ጢሞ፤1:15

የምሥራቹ ቃል ክርስቶስ የሞተው ለእንደኛ ኃጢአተኞች መሆኑን ይነግረናል፡፡የዘላለምን ሕይወትን እና ደስታን ሊሰጠን ሞተ፡፡ በሞቱም የመዳንን ኃይል አድሶ በአካል ከሞት ተነሣ (1ኛ ቆሮ፡15፤20)።

ይህም ማለት ኃጢአተኞችን በነፃ ለቆ ፃድቅና ፍጹም መሆን ይችል ነበር ነገር ግን የፍቅሩን ጥልቀት ለመግለጽ እርሱ ሞተልን።ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻዲቅ ሆኖ ሳለ ስለ አመጻኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና (1ኛ ጴጥሮስ 3፡18)።

## 6 በክርስቶስ ሞት የተገዛው ህይወት የሚጠቅመው ንስሐ ለሚገቡና በርሱ ለሚታመኑት ነው።

ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሓ ግቡና ተመለሱም፡፡
የሐዋርያት ሥራ 3፤19
በጌታ እየሱስ እመኑ እናም ትድናላችሁ (የሐዋ፡ሥራ 16:31)

‹ ንስሐ ›መግባት ማለት ከውሸት የኃጢአት ማባበል መመለስ ማለት ነው።እየሱስ በኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ  አይጠማም ብሎዋል (ዮሐንስ 6:35)፡፡ነገር ግን መዳናችንን ሰርተን ያገኘነው ነገር አይደለም፡፡መዳናችን አይገባንም (ሮሜ፡4፤4-5)፡፡እኛ የዳንነው በእምነት በሚገኘው በእግዚአብሔር ፀጋ ነው (ኤፌ 2:8-9)፡፡ የተቀበልነውም ነፃ ስጦታ ነው(ሮሜ፡3፤24) ፡፡ደህንነታችን የኛ የሚሆነው ከሁሉ በላይ አድርገን ከፍተኛ ዋጋ ከሠጠነው ብቻ ነው (ማቴ 13፤44)፡፡ያንን ካደረግን የእግዚአብሔር ዓላማ በፍጥረቱ ይፈጸማል፤ ለዘላለምም በኛ ይከብራል፤እኛም  በርሱ ደስ ይለናል።

desiringGod

P.O. Box 2901
Minneapolis, MN 55402 USA
Sin Cargo: 1.888.346.4700 Fax: 1.612.338.4372
Email: mail@desiringGod.org Web: www.desiringGod.org

Product code: TAMQFJ

# እውነተኛ ደስታን መፈለግ

# እግዚአብሔር ደስታን እንድንፈልግ እንዳዘዘን ታውቃለህ?